ሠላሳ አራተኛ ዓመት ቍጥር ፵፩
34th Year — No. 41

አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፱ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ. ም.
Addis Ababa, 26th July, 1975

የኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት

ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ።
NEGARIT GAZETA

የጋዜጣው ፡ ዋጋ ፡	በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ሊቀ መንበር ጽሕፈት ቤት ተጠባባቂነት የወጣ	ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ይታተማል ።
ባገር ፡ ውስጥ ፡ ባመት ፡ $ 6		የፖስታ ሣጥን ቍጥር ፩ሺ፴፩ (1031)
» » በ፮ ፡ ወር ፡ $ 3		
» » ያንዱ ፡ $ 1		

ማውጫ
፲፱፻፷፰ ዓ. ም.

አዋጅ ቍጥር ፵፯/፲፱፻፷፯ ዓ. ም.
የከተማን ቦታና ትርፍ ቤት የመንግሥት ንብረት ለማድረግ የ[illegible]ጣ አዋጅ . . . . . ገጽ ፪፻

CONTENTS
1976

Proclamation No. 47 of 1975
Government Ownership of Urban Lands and Extra Houses Proclamation . . . . Page 200

አዋጅ ቍጥር ፵፯/፲፱፻፷፯ ዓ. ም.

[illegible]ማን ቦታና ትርፍ ቤት የመንግሥት ንብረት ለማድረግ [illegible] አዋጅ

«ኢት[illegible]ጵያ [illegible]ደም»

በየከተማዎቹ ውስጥ በሚገኙት ፋብሪካዎች [illegible] ትሪዎችና እንዲሁም በየከተሞች ውስጥ በሚገኙ በተለያዩ የሥራ መስኮች ተሠማርቶ የሚገኘው የከተማው ወዝ አደርና ለፍቶ አዳሪው በኅብረተሰቡ ውስጥ ሊኖረው የሚችለው የኑሮ ደረጃ ፤ ሰብአዊ መብቱ ፤ ክብሩና ማዕርጉ የሚወሰነው የሚኖርባት ከተማ በምትሰጠው የመኖርና የመሥራት ዕድል በመሆኑ ፤

በከተሞቻችን ውስጥ አብዛኛዎቹ ቦታዎችና ቤቶች በጥቂት መሣፍንት ፤ መኳንንት ፤ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣኖችና በከበርቴዎች በመያዛቸው ፤ እነዚህም የሀብታም ክፍሎች ያላቸውን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ኃይል ያለአግባብ በመጠቀም ሰው ሠራሽ የከተ[illegible] ቦታ እጥረት በመፍጠር የከተማ [illegible]ዋጋን እንዲወደድ በ[illegible]ድረግ ፤ በጠቅላላው የብዝበዛ ሥር[illegible]ትንሀር ለከተማው እድገትና ለብዙኃኑ የከተማ ነዋሪ [illegible] የኑሮ መሻሻል ከ[illegible]ተኛ እንቅፋት በመሆናቸው ፤

ለመኖሪያ የሚያገለግ[illegible]ም ሆነ ለመሥሪያ የሚሆነው የከተማ ቤት በጥቂት ሰዎች እጅ መሆኑ የቤት ኪራይ ቁጭ ብለው ሳይለፉ በማግኘት ሰፊ ብዝበዛ እንዲፈጽሙ ከማስቻሉም በላይ ፤ ከእነዚህም [illegible]ካከል ከሕግ በላይ ሆነው ለብዙ ዘመናት የግብር ክፍያ [illegible]ዴታቸውን እንዳያሟሉ ስላደረጋቸው ፤

በከተማ የሚኖረው ወዝ አደርና ለፍቶ አዳሪው ለረጅም ዘመን ግፍና ጭቆና እየተፈጸመበት ለገዥው መደብ ቅንጦትና መንደላቀቅ መሣሪያ በመሆን ፤ የጭቆና አገዛዝ ተጭኖት የኢትዮጵያዊነቱን መብት ተገፍፎ ለብዙ ዘመን አጥቶት የነበረውን አገሩ በእኩልነት ልትሰጠው የሚገባውን የኢኮኖሚ፤ የፖለቲካና የስሻል መብቱ እንዲጎናጸፍ ለማድረግ ፤ የሚኖርባት ከተማ የምትሰጠውን ማንኛውንም ዕድል በእኩልነት እንዲያገኝ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ ፤

PROCLAMATION No. 47 OF 1975

A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR GOVERNMENT OWNERSHIP OF URBAN LANDS AND EXTRA URBAN HOUSES

"ETHIOPIA TIKDEM"

WHEREAS, [illegible] standard of living, rights, honour and status of workers and toiling [illegible] in industries and other fields of activity are determined by the [illegible] to which the urban areas in which they live afford opportunities of work and shelter;

WHEREAS, extensive areas of urban land and numerous houses are in the hands of an insignificant number of feudal lords, aristocrats, high Government officials and capitalists, who by abusing their political and economic power, have created artificial shortages in the supply of urban land, thereby inflating its value and obstructing the improvement of urban areas and of the quality of life of urban dwellers in their effort to perpetuate the system of exploitation;

WHEREAS, the concentration of urban houses suitable both for dwelling and business purposes in the hands of a few individuals has not only enabled such people to carry on their exploitation of the many through house rent but has also led them to place themselves above the law and to evade their duty to pay taxes for a long time;

WHEREAS, the urban-dwelling workers and other toiling masses, forced to languish for a long time under the yoke of subjugation and oppression and used as mere instruments for the furtherance of the comfort and luxury of the ruling class, can regain their rights as Ethiopians, that is, their economic, political and social rights which should have been made equally available to them by their country but which were denied them for a long time, only when all the opportunities afforded by the urban center in which they live are open to them on the basis of equality;

SAMUEL GIRMA

በቤት ኪራይ ላይ ቁጥጥር ባለመኖሩ ኪራይ በየጊዜው እየናረ በመሔዱ ፤ የሰፊው የከተማ ሕዝብ ኑሮ በአሳዛኝ ሁኔታ ላይ በመውደቁ ፤

ከተሞቻችን ለብዙኃኑ የከተማ ነዋሪ ሕዝብ ለመኖሪያ ወም ሆነ ለመሥሪያ እንዲመች አድርጎ በፕላን ለመቀየስ እንዲቻል ፤

ከዚህ በፊት ከየባንኮችና ከኢንሹራንስ ኩባንያዎች የመበደር ዕድል የነበረው ክፍል (ትና ቦታ ዋስትና ለመስጠት የሚችል ብቻ በመሆኑ ፤ ሰፊው የከተማ ሕዝብ ይህንን ጠቃሚ የብድር አገልግሎት ለማግኘት ባለመቻሉና ይህንንም የመበደር መብት ሰፊው ሕዝብ እን ያገኘው ለማድረግ ፤

በከተማ የሚኖረውን ሰፊ ሕዝብ ከከፍተኛ የኪራይ ሸክም በማዳን ፤ አስፈላጊውን የብድር ዕርዳታና ለመኖሪያም ሆነ ለመሥሪያ ቤት መሥሪያ የሚሆነውን ቦታ በመስጠት የኑሮውን ሁኔታ በማሻሻል ለአገሩ ፤ ለወገኑ ፤ ለቤተሰቡና ለራሱ በልበሙሉነት እንዲሠራ ለማድረግ ፤

ከተሞቻችንን በዕቅድና በጥናት እንዲሠሩ ማድረግ የአገሪቱ ሀብት በሚገባ በቁጠባ ጥቅም ላይ እንዲውል ፤ የከተማን ሁኔታ ለማሻሻል ፤ ነዋሪውን ከበሽታ ለማዳንና በከተማ የሚፈጸሙትን ሕገ ወጥ ተግባሮች ለማጥፋት የሚያስችል መሆኑን በማመን ፤

የከተሞቻችን ቦታና ቤት ይዞታ በፍርድ ቤቶች በኩል ያስከተለውን ማለቂያ የሌለው ክርክር በማስቀረት ሀብትና ጉልበት እንዳይባክን ለማድረግ ፤

በከተሞቻችን ውስጥ መደሪያና መጠጊያ ሊያገኙ ላልቻሉት አስፈላጊ ዕርዳታዎች መስጠት ለመጀመር ፤

በከተማው ሕዝብ መካከል ያለውን ያልተመጣጠነ ሀብትና ገቢ እንዲሁም አገልግሎት አጥጋቢ በሆነ ሁኔታ በማደላደል አሁን ያለውን ከፍተኛ የኑሮ መራራቅ ለማቀራረብ ፤ ያንዱ ብልጽግና በሌላው መቆርቆዝ ላይ እንዳይመሠረት ለማስቻል የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት የመንግሥት ንብረት እንዲሆን ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ ፤

የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግንና የሊቀ መንበሩን ሥልጣን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፪/፲፱፻፷፯ ዓ. ም. በአንቀጽ ፮ መሠረት ከዚህ የሚከተለው ታውጇዋል ።

ምዕራፍ ፩

መግቢያ

፩ ፤ አጭር ርእስ ፤

ይህ አዋጅ « የከተማን ቦታና ትርፍ ቤት የመንግሥት ንብረት ለማድረግ የወጣው አዋጅ ቁጥር ፵፯/፲፱፻፷፯ ዓ. ም. ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪ ፤ ትርጓሜ ፤

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ ፤

፩/ « የከተማ ቦታ » ማለት በማዘጋጃ ቤት ወይም በከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ መሬት ነው ።

፪/ « የከተማ ቤት » ማለት ተሠርቶ ያለቀ ወይም በጅምር ላይ ያለ ለመኖሪያ ፤ ለሥራ ወይም ለሌላ አገልግሎት የሚውል ቤት ነው ።

፫/ « ትርፍ ቤት » ማለት ፦

ሀ) አንድ ቤተሰብ ወይም ግለሰብ ለመኖሪያ ከሚያስፈልገው ወይም ከያዘው ከአንድ መኖሪያ ቤት በላይ ፤ ወይም

WHEREAS, the absence of control on rent of houses and the consequent soaring up of rents has rendered the lives of the masses of urban dwellers miserable;

WHEREAS, it is necessary to survey and plan our cities with the need for dwelling and working purposes of the majority of city dwellers as the prime factor;

WHEREAS, until now, only that class of people who could produce as security their ownership title of urban land or house benefited from the facilities afforded by banks and insurance companies which the broad urban dwellers were denied, and it is now necessary to make such credit facilities available to such broad masses;

WHEREAS, it is necessary to lighten the burden of paying high house rents of the broad urban dwelling masses, provide them with the necessary credit facilities, and make available to them urban lands for the construction of both dwelling and business houses, thereby improving their standard of living and creating for them the conditions to fruitfully work in confidence for their country, their families and themselves;

WHEREAS, it is necessary to build our urban areas on the basis of careful planning and study in order to utilize our resources in an economical manner, to improve the conditions of cities, to protect urban dwellers from diseases and prevent illegal acitivities now prevalent in urban areas;

WHEREAS, it is necessary to do away with the inexhaustible court cases involving urban lands and houses thereby saving valuable financial and human resources from wastage;

WHEREAS, it is necessary to provide help to those people in urban areas who cannot afford to have shelters of their own;

WHEREAS, in order to bridge the wide gap in the standard of living of urban dwellers by appropriate allocation of disproportionately-held wealth and income as well as the inequitable provision of services among urban dwellers and to eliminate the exploitation of the many by the few, it is necessary to bring under Government ownership and control urban lands and extra urban houses;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 6 of the Definition of Powers of the Provisional Military Administration Council and its Chairman Proclamation No. 2/1974, it is hereby proclaimed as follows:

CHAPTER I

INTRODUCTION

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Government Ownership of Urban Lands and Extra Houses Proclamation No. 47/1975".

2. *Definitions*

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:

1/ "urban lands" shall mean all lands within the boundaries of a municipality or a town;

2/ "urban house" shall mean any house whether fully constructed or under construction intended for dwelling or business or other purposes.

3/ "extra house' 'shall mean an urban house whether rented or used or otherwise owned, other than:

a) a single house required or occupied as a dwelling place by a person or family;

SAMUEL GIRMA

ምዕራፍ ፪

ስለ ከተማ ቦታ

፫ ፤ የከተማ ቦታ የመንግሥት ስለማድረግ ፤

፩/ ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን ጀምሮ የከተማ ቦታ የመንግሥት ንብረት ሆኗል ።

፪/ ማንኛውም ቤተሰብ ፤ ግለሰብ ወይም ድርጅት የከተማ ቦታ በግል ባለሀብትነት ለመያዝ አይችልም ።

፫/ ለከተማ ቦታ ካሣ አይከፈልም ።

፬ ፤ የከተማ ቦታ ማስተላለፍ ስለመከልከሉ ፤

፩/ የከተማ ቦታ ሊሸጥ ፤ በወለድ አግድ ሊሰጥ ወይም በዕዳ ሊያዝ ፤ በውርስ ወይም በሌላ መንገድ ሊተላለፍ አይችልም ።

፪/ ከታኅሣሥ ፲፩ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. ጀምሮ የከተማን ቦታ በስጦታ ፤ በውርስ ፤ በጭሰኝነት ፤ በሽያጭ ወይም በሌላ መንገድ ለማስተላለፍ የተደረገ ተግባር ወይም ውል ተሽሯል ።

፭ ፤ የይዞታ መጠን ስለመወሰን ፤

፩/ አንድ ቤተሰብ ወይም ግለሰብ ለመኖሪያ ቤት መሥሪያ የሚያውለው እስከ አምስት መቶ (፭፻) ካሬ ሜትር የሚደርስ የከተማ ቦታ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መምሪያ መሠረት በይዞታ ሊሰጠው ይችላል ። ባለይዞታው ሲሞት የሟች ሚስት ወይም ባል ወይም ልጆች በይዞታው ተተክተው የመጠቀም መብት ይኖራቸዋል ።

፪/ አንድ ድርጅት ለመኖሪያ ቤት ወይም ለመሥሪያ ቤት መሥሪያ የከተማ ቦታ እንዲሰጠው ሲያመለክት ሚኒስቴሩ አስፈላጊነቱን ሲያምንበት መጠኑን በሚወስነው መሠረት በይዞታ ሊሰጠው ይችላል ።

፫/ ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ፤ ለመሥሪያ ቤት ወይም ለሠራተኞች መኖሪያ ቤት መሥሪያ እንዲውል በግለሰብ ፤ በቤተሰብ ወይም በድርጅት የተያዘ የከተማ ቦታ መጠን በሚኒስቴሩ ይወሰናል ።

፮ ፤ ስለ ከተማ ቦታ ጭሰኛ ይዞታ ፤

፩/ በከተማ ባለርስትና በከተማ ጭሰኛ መካከል ያለው ግንኙነት ፈርሷል ። ጭሰኛው ለከተማ ባለርስት ከሚከፍለው ኪራይና ሌላ ክፍያ እንዲሁም ከማንኛውም አገልግሎትና ዕዳ ነፃ ሆኗል ።

፪/ በአንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በአንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው የይዞታ መጠን ማንኛውም ጭሰኛ በያዘው የከተማ ቦታ ላይ የይዞታ መብት ይኖረዋል ።

፯ ፤ የይዞታ ቅድሚያ ወይም መብት ስለመስጠት ፤

፩/ ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የከተማ ቦታ ያለው ቤተሰብ ፤ ወይም ግለሰብ ሌላ የመኖሪያ ቤት ከሌለው በአንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በአንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው የይዞታ መጠን በቦታው ላይ የይዞታ መብት ይኖረዋል ።

CHAPTER II

URBAN LANDS

3. *Government Ownership of Urban Lands*

1/ As of the effective date of this Proclamation, all urba lands shall be the property of the Government.

2/ No person, family or organization shall hold urba land in private ownership.

3/ No compensation shall be paid in respect of urba lands.

4. *Prohibition of Transfer of Urban Land*

1/ No urban land may be transferred by sale, antichres mortgage, succession or otherwise.

2/ Any transfer of urban land by donation, successio lease, sale or otherwise made as of Tahsas 11, 196 shall be null and void.

5. *Size of Holding*

1/ Any person or family may, in accordance with dir tives issued by the Ministry, be granted the possessi of urban land upto 500 square meters for the purp of building a dwelling house. Upon the death of holder the wife or husband or children shall have right to use the land.

2/ Where an organization applies to the Ministry to granted urban land for building a dwelling or busin house the Ministry may, on being satisfied of need, grant such land in sizes to be determined it.

3/ The Ministry shall determine the size of urban la held before the effective date of this Proclamation a person, family or an organization for the purp of building dwelling houses for his or its employ or for building business houses.

6. *Urban Tenant's Holding*

1/ The relationship between landowners and tenants urban land is hereby abolished. The tenant shall free from payment to the landowner of rent, debt any other obligation.

2/ Subject to Article 4 (2) and within the limit of size mentioned in Article 5 (1), the tenant shall h possessory right over the land he holds.

7. *Granting of Rights of Possession or Priority*

1/ Subject to Article 4 (2) and within the limit of size mentioned in Article 5 (1), any person who family which does not own a dwelling house shall ha possessory right over the land which he or it hol before the effective date of this Proclamation.

SAMUEL GIRMA

ለ) አንድ ድርጅት ለሠራተኞቹ ወይም በኃላፊነቱ ለሚያስተዳድራቸው ሰዎች ለመኖሪያ ቤት ከሚያስፈልገው ወይም ከያዘው በላይ ፤ ወይም

ሐ) አንድ ቤተሰብ ፤ ግለሰብ ወይም ድርጅት ለሥራው ከሚያስፈልገው መሥሪያ ቤት በላይ ፤ የሆነ የኪራይ ገቢ ወይም ሌላ ጥቅም ለማስገኘት ወይም ያለጥቅም የተያዘ የከተማ ቤት ነው ።

፬/ « የመኖሪያ ቤት » ማለት አንድ ቤተሰብ ወይም ግለሰብ ለራሱ ወይም አንድ ድርጅት ለሠራተኞቹ ወይም በኃላፊነቱ ለሚያስተዳድራቸው ሰዎች መኖሪያ የሚያውለው የከተማ ቤት ነው ።

፭/ « የመሥሪያ ቤት » ማለት አንድ ቤተሰብ ፤ ግለሰብ ወይም ድርጅት ለሥራ የሚጠቀምበት የከተማ ቤት ወይም የከተማ ቦታ ነው ።

፮/ « አከራይ » ማለት ከከተማ ቦታ ወይም ቤት ኪራይ የሚያገኝ ቤተሰብ ፤ ግለሰብ ወይም ድርጅት ነው ።

፯/ « ተከራይ » ማለት ኪራይ እየከፈለ በሌላ ቤተሰብ ፤ ግለሰብ ወይም ድርጅት የከተማ ቦታ ወይም የከተማ ቤት የሚጠቀም ነው ።

፰/ « ደባል » ማለት በአንድ የመኖሪያ ቤት ውስጥ አብሮ እየኖረ ለአከራዩ ወይም ለተከራዩ ኪራይ የሚከፍል ቤተሰብ ወይም ግለሰብ ነው ።

፱/ «ጭሰኛ » ማለት ኪራይ እየከፈለ ወይም አገልግሎት እየሰጠ በሌላ ቤተሰብ ፤ ግለሰብ ወይም ድርጅት የከተማ ቦታ ላይ ፤ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ቤት በመሥራት ወይም ለሌላ አገልግሎት በማዋል የሚጠቀም ነው ።

፲/ «ኪራይ » ማለት የከተማ ቦታን ወይም የከተማ ቤትን በማከራየት የሚገኝ ገንዘብ ወይም ሌላ ጥቅም ነው ።

፲፩/ « የወለድ አግድ ይዞታ » ማለት በዕዳ ዋስትና በአበዳሪ ወይም በውል በተጠቀሰው ሰው የተያዘ የከተማ ቤት ወይም የከተማ ቦታ ነው ።

፲፪/ «የመጠቀም መብት » ማለት የከተማ ቦታን ማውረስን ፤ በስጦታ ማስተላለፍን ፤ በዕዳ ማስያዝን ወይም መሸጥን የማይጨምር በግል የመጠቀም መብት ነው ።

፲፫/ « ድርጅት » ማለት በንግድ ሕግ ፤ በፍትሐ ብሔር ሕግ የተቋቋመ ድርጅትና እንዲሁም በፍትሐ ብሔር ሕግ ቍጥር ፫፻፺፰ የተመለከተው ድርጅት ነው ።

፲፬/ « የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር » ማለት በዚሁ አዋጅ በምዕራፍ ፭ መሠረት የሚቋቋም ማኅበር ነው ።

፲፭/ « ሚኒስትር » ማለት የሥራና የቤቶች ሚኒስትር ነው ።

፲፮/ « ሚኒስቴር » ማለት የሥራና የቤቶች ሚኒስቴር ነው ።

፲፯/ « የከተማ ቦታና ቤት ነክ ክርክር » ማለት በከተማ ቤት ላይ የንብረትነትን ፤ የማውረስን ፤ የይዞታን ፤ የኪራይን ወይም የመጠቀምን መብት የሚመለከት ክርክር ነው ። እንዲሁም የከተማ ቦታ ይዞታን ክርክርም ይጨምራል ።

b) houses required or occupied by an organization as dwelling places for its employees or persons under its responsibility;

c) houses required for running the business of a person, family or an organization.

4/ "dwelling house" shall mean an urban house used for dwelling by a person or family or the emplyees of an organization or persons under its responsibility.

5/ "business house" shall mean an urban house or space used for running the business of a person or family or an organization.

6/ "lessor" shall mean a person who or a family or an organization which rents out an urban land or house.

7/ "lessee" shall mean a person who or a family or an organization which pays rent for the use of an urban land or house.

8/ "co-dweller" shall mean a person who or a family which dwells with a lessor or lessee in the same dwelling house and pays rent to the lessor or lessee.

9/ "tenant" shall mean a person who or a family or an organization which pays rent gives any other consideration for the use of urban land, for a limited or unlimited time, irrespective of the use to which suchds land is put.

10/ "rent" shall mean the money or other considerati paid to a lessor for the use of an urban land or hou

11/ "holding in antichresis" shall mean an urban land the house held by the lender or other person agreed to be in the contract as security for a debt.

12/ "use-right" shall mean the right to personal use, but in respect of urban land, shall not include the right to transfer it by will, donation, mortgage or sale.

13/ "organization" shall mean any organization or association provided for in the Commercial Code or Civil Code and shall include the body referred to in Art. 398 of the latter.

14/ "co-operative society of urban dwellers" shall mean a co-operative society to be established under Chapter V of this Proclamation.

15/ "Minister' 'shall mean the Minister of Public Works and Housing.

16/ "Ministry" shall mean the Ministry of Public Works and Housing.

17/ "dispute involving urban land and house" shall mean a dispute over the ownership, succession, possession, lease or use of urban house and shall include disputes over the possession of urban land.

SAMUEL GIRMA

፪/ ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የከተማ ቦታ ለመግዛት በቅድሚያ በሙሉም ሆነ በከፊል ገንዘብ የከፈለ ማንኛውም ቤተሰብ ወይም ግለሰብ ሌላ የመኖሪያ ቤት ከሌለው በአንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በአንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው የይዞታ መጠን በዚሁ ቦታ ላይ የይዞታ ቅድሚያ ይኖረዋል ።

፫/ በአንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና በአንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የከተማ ቦታ ያለው ድርጅት በቦታው ላይ የይዞታ መብት ይኖረዋል ፤ እንዲሁም ለመግዛት በቅድሚያ በሙሉም ሆነ በከፊል ገንዘብ የከፈለ ማንኛውም ድርጅት የይዞታ ቅድሚያ ይኖረዋል ።

፰ ፤ የከተማ ቦታ መልሶ ስለመውሰድ ፤

፩/ የከተማ ቦታ የያዘ ቤተሰብ ፤ ግለሰብ ወይም ድርጅት ሚኒስቴሩ በሚወስነው ጊዜ ውስጥ በሥራ ላይ ካላዋለው ሚኒስቴሩ ቦታውን መልሶ በመውሰድ አስፈላጊ በመሰለው ጥቅም ላይ ያውለዋል ።

፪/ በቤተሰብ ፤ በግለሰብ ፤ ወይም በድርጅት የተያዘ የከተማ ቦታ መንግሥት ለሕዝብ አገልግሎች ለማዋል የሚያስፈልገው ሲሆን ሚኒስቴሩ ንጣፍ እየሰጠ ቦታውን ሊወስድ ይችላል ።

፱ ፤ ስለከተማ ቦታ ኪራይ ፤

ማናቸውም ቤተሰብ ፤ ግለሰብ ፤ ወይም ድርጅት በያዘው የከተማ ቦታ መንግሥት በሚወስነው መሠረት የከተማ ቦታ ኪራይ ይከፍላል ።

፲ ፤ በከተማ ክልል ውስጥ ስለተተከሉ ዛፎች ፤

በከተማ ውስጥ በአንቀጽ ፭ ከተጠቀሰው የቦታ መጠን ውጪ የተተከሉ ዛፎች የመንግሥት ንብረት ሆነዋል ።

ምዕራፍ ፫

ስለ ከተማ ቤት

፲፩ ፤ የመሥሪያ ቤትና የመኖሪያ ቤት ስለመያዝ ፤

፩/ አንድ ቤተሰብ ወይም ግለሰብ በሚመርጥበት አንድ ከተማ ብቻ አንድ የመኖሪያ ቤት ሊኖረው ይችላል ።

፪/ መንግሥት በሚወስነው መሠረት አንድ ድርጅት ለሠራተኞቹ ወይም በኃላፊነት ለሚያስተዳድራቸው ሰዎች ለመኖሪያ የሚሆን ቤት ሊኖረው ይችላል ።

፫/ አንድ ቤተሰብ ፤ ግለሰብ ፤ ወይም ድርጅት እንደ ሥራው ሁኔታና ዓይነት መንግሥት በሚወስነው መሠረት የመሥሪያ ቤት ሊኖረው ይችላል ።

፬/ መጠኑን መንግሥት በሚወስነው መሠረት ፤ ማናቸውም መኖሪያ ቤት ወይም መሥሪያ ቤት ያለው ቤተሰብ ፤ ግለሰብ ወይም ድርጅት ግብር ይከፍላል ።

፲፪ ፤ የከተማ ቤት ስለማስተላለፍ ፤

፩/ አንድ ቤተሰብ ፤ ግለሰብ ወይም ድርጅት በከተማ ቤቱ የመጠቀም ወይም ይህንኑ ቤት የማውረስ ፤ የመሸጥ ወይም የመለወጥ መብት አለው ። ሆኖም ሽያጭ ከሆነ መንግሥት የግዥ ቀደምትነት መብት ይኖረዋል ።

2/ Subject to Article 4 (2) and within the limit of the size mentioned in Article 5 (1), any person who or family which has paid in full or in part before the effective date of this Proclamation the purchase price of an urban land but does not own a dwelling house shall have priority over the possession of such land.

3/ Subject to Articles 4 (2) and 5 (2), an organization which owns urban land before the effective date of this Proclamation shall have possessory right over such land. Where such organization has paid in full or in part the purchase price of urban land, it shall have priority over the possession of such land.

8. *Power of Taking and Expropriation*

1/ Where a person, family or an organization fails to utilize his or its urban land within the period to be specified by the Ministry, the Ministry may take back such land and put it to appropriate use.

2/ The Ministry shall, by giving compensation in kind, expropriate for public purpose urban land held by a person, family or an organization.

9. *Urban Land Rent*

Any person who or family or organization which holds urban land shall pay rent to be fixed by the Government.

10. *Ownership of Trees in Urban Areas*

Trees on urban lands other than those on lands within the limit of the size mentioned under Article 5 shall be Government property.

CHAPTER III

URBAN HOUSES

11. *Dwelling and Business Houses*

1/ Any person or family may own only a single dwelling house in any urban area of his choice.

2/ Any organization may own houses for the purpose of housing its employees or persons under its responsibility, the number and size of which shall be determined by the Government.

3/ Any person, family or organization may own business houses the number and size of which shall be determined by the Government taking into account the condition and type of business.

4/ Any person, family or organization shall pay taxes on his or its dwelling or business houses at rates to be determined by the Government.

12. *Transfer of Urban Houses*

1/ Any person, family or organization may use his or its own house or transfer such house by succession, sale or barter. However, in case of sale the Government shall have right of pre-emption.

፪/ ከታኅሣሥ ፲፩ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. ጀምሮ የከተማን ቤት በንብረትነት የያዘ ቤተሰብ ፣ ግለሰብ ፣ ወይም ድርጅት መብቱ በሚኒስቴሩ ካልጸደቀለት በስተቀር ንብረትነቱ አይጸናለትም ። ሚኒስቴሩም ንብረትነቱን የሚያጸድቀው የዚህን አዋጅ ዓላማ የማይቃረን ሆኖ ሲያገኘው ብቻ ነው ።

፲፫ ፣ የከተማን ትርፍ ቤት የመንግሥት ስለማድረግ ፤

፩/ በአንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፣ (፪) እና (፫) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በማዘጋጃ ቤት ወይም በከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ ትርፍ ቤት ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን ጀምሮ የመንግሥት ንብረት ሆኗል ።

፪/ ማንኛውም ቤተሰብ ፣ ግለሰብ ወይም ድርጅት ያለውን ትርፍ የመኖሪያ ቤትና የመሥሪያ ቤት ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን ጀምሮ በሠላሳ ቀን ውስጥ ለሚኒስቴሩ የማስታወቅ ፣ የማስመዝገብና ፣ የማስረከብ ግዴታ አለበት ።

፲፬ ፣ ከመንግሥት ስለተወሰዱ ቤቶች ፤

፩/ የመንግሥት ወይም ቀድሞ የጠላት ንብረት የነበሩ ወይም በሕዝብ ወይም በመንግሥት ገንዘብ የተሠሩ ቤቶች በግል ቤተሰቦች ወይም ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች በስጦታ ወይም በማይመጣጠን አነስተኛ ዋጋ የተሸጡ ወይም በተመሳሳይ ሁኔታ የተሰጡ ቤቶች ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን ጀምሮ የመንግሥት ንብረት ሆነዋል ። ይህ ንዑስ አንቀጽ ለሦስተኛ ወገኖች በተላለፉም ቤቶች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል ።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተወሰደ ቤት ለሦስተኛ ወገን የተላለፈ ከሆነና ሦስተኛውም ወገን የከፈለው ገንዘብ ከቤቱ ዋጋ ጋር ተመጣጣኝ ካልሆነና ትርፍ ቤት ከሌለው ልዩነቱን ለመንግሥት ከፍሎ የቤቱን ንብረትነት ሚኒስትሩ ሊያጸናለት ይችላል ።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተወሰደው ቤት ለሦስተኛ ወገን የተላለፈ ከሆነ፣ሦስተኛውም ወገን የከፈለው ገንዘብ ከቤቱ ዋጋ ተመጣጣኝ ከሆነና ቤቱም ትርፍ ካልሆነ ሚኒስትሩ የቤቱን ንብረትነት ሊያጸናለት ይችላል ።

፬/ ማንኛውም ሰው የከተማን ቤት ከመንግሥት በስጦታ ወይም በማይመጣጠን አነስተኛ ዋጋ ወስዶ በመሸጥ የተጠቀመና ቤቱም በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) መሠረት ከገዢው ያልተወረሰ እንደሆነ ሻጩ ዋጋውን ለሚኒስቴሩ የመክፈል ግዴታ አለበት ።

፲፭ ፣ ለአካለ መጠን ባልደረሰ ሰው የተያዘ ቤት ፤

ከወላጁ ፣ ከአስተዳዳሪው ወይም ከአሳዳጊው ጋር የሚኖር ለአካለ መጠን ያልደረሰ ሰው የሚያከራየው ወይም ሊያከራይ የሚችለው የከተማ ቤት የመንግሥት ንብረት ሆኗል። ሆኖም ወላጁ የራሱ የከተማ ቤት ከሌለው ለአካለ መጠን ያልደረሰው ሰው በአንቀጽ ፲፩ በንዑስ አንቀጽ (፩) በተሰጠው መብት መጠቀም ይችላል ።

2/ No right in ownership of urban houses acquired as of Tahsas 11, 1967 shall be effective unless validated by the Ministry. In validating such right the Ministry shall ascertain that the acquisition does not contradict the purposes of this Proclamation.

13. *Government Ownership of Extra Houses*

1/ Subject to Article 11 (1), (2) and (3), all extra houses within the boundaries of a municipality or town shall, on the effective date of this Proclamation, be Government property.

2/ Any person who or family or organization which owns an extra house shall have the obligation to notify, register with and hand over to the Ministry such extra house within 30 days from the effective date of this Proclamation.

14. *Houses Taken from the Government*

1/ Urban houses which belonged to the Government or which were enemy property or houses built with funds raised by the public or obtained from the Government and were donated, sold at depressed prices or transferred to a person, family or an organization under similar circumstances shall, on the effective date of this Proclamation, be Government property. The foregoing provision shall also apply to said houses which have since been transferred to third parties.

2/ Where the house mentioned in the above sub-article has been transferred to another and where the purchase price paid for it is unreasonably low compared to the actual price, the Minister may permit the transferree having no extra house to retain the ownership of such house upon payment of the difference.

3/ Where the house mentioned in sub-article (1) of this Article has been transferred to another and where the purchase price paid for the house is roughly equal to the actual price, the Minister may permit the transferee having no extra house to retain the house.

4/ Where a person who had acquired a house belonging to the Government by donation or by paying a depressed price and has sold such house and the house is not taken by the Government under sub-articles (2) and (3) of this Article, such person shall pay to the Ministry an amount equal to the price he obtained from the transaction.

15. *Houses Owned by Minors*

Any urban house which a minor living with his parent, guardian or tutor has leased out or which is capable of being leased shall be Government property. However, where the parent does not own an urban house, the minor may exercise the right given under Article 11 (1).

SAMUEL GIRMA

፲፮ ፤ ወደግል ቤት ስለመመለስ ፤

፩/ የራሱ የከተማ ቤት እያለው በማናቸውም ሁኔታ በሌላ ቤት የሚኖር ቤተሰብ ወይም ግለሰብ ወደግል ቤቱ ፤ ወይም ከአንድ የከተማ ቤት በላይ ያለው ቤተሰብ ወይም ግለሰብ ወደሚመርጠው ቤት ለመመለስ መብት አለው ። ሆኖም ቤቱ ለመሥሪያ ቤትነት አስፈላጊ መሆኑን ወይም ከአንድ ቤተሰብ በላይ በመኖሪያ ቤትነት ለማስፈር የሚችል መሆኑን ሚኒስቴሩ ሲያረጋግጥ ይህ ንዑስ አንቀጽ ተፈጻሚነት አይኖረውም ። ቤቱንም መንግሥት ይወርሰዋል ።

፪/ በወለድ አግድ በሌላ ሰው የተያዘ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የመሥሪያ ቤት ያለው ሰው ፤ ሌላ መሥሪያ ቤት የሌለው ከሆነ ለሚሠራው ሥራ ሕጋዊ ፈቃድ ይዞ ወደሚመርጠው ቤት ለመግባት መብት አለው ። ሆኖም ቤቱ በመሥሪያ ቤትነት ለማገልገል የማይችል መሆኑን ሚኒስቴሩ ሲያረጋግጥ ይህ ንዑስ አንቀጽ ተፈጻሚነት አይኖረውም ፤ ቤቱንም መንግሥት ይወርሰዋል ።

፫/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፬) የተወሰነውን ማስጠንቀቂያ በመስጠት አንድ ቤተሰብ ወይም ግለሰብ በደባልነት የሚኖረውን ተከራይ የማስለቀቅ መብት አለው ።

፬/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) መሠረት ወደከተማ ቤቱ ለመመለስ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ቤቱን ለያዘው ሰው በጽሑፍ ከስድስት ወር ጊዜ ያላነሰ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል ።

፭/ በአንቀጽ ፳ ንዑስ አንቀጽ (፬) እና አንቀጽ ፳፩ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፤ (፫) ፤ እና (፬) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተከራዩ ቤቱን እስካስረከበ ድረስ የቤቱን ኪራይ የሚከፍለው ለሚኒስቴሩ ወይም ለከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር ነው ።

፮/ አንድ ቤተሰብ ወይም ግለሰብ በሥራ ምክንያት አዘውትሮ ከሚኖርበት ከተማ የለቀቀ ወይም የተዛወረ እንደሆነና ቀድሞ በሚኖርበት ከተማ የራሱ መኖሪያ ቤት ያለው ከሆነ ፤ በመልቀቁ ወይም በመዛወሩ ምክንያት ቤት ለመከራየት የሚያስከትልበትን ችግር ማስወገጃ እንዲሰጠው ሲያመለክት ሚኒስቴሩ ወይም የኅብረት ሥራ ማኅበሩ የቤቱን አስተዳደር ተረክቦ እንደ አካባቢው የኑሮ ሁኔታ ተመጣጣኝ መኖሪያ ቤት ፤ ወይም ወጪ እየሰጠ በሚመለስበት ጊዜ ቤቱን መልሶ ያስረክበዋል ።

፲፯ ፤ በወለድ አግድ ስለተያዙ ቤቶች ፤

፩/ ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን ጀምሮ ቤትን በሚመለከት ረገድ የወለድ አግድ ውል ተሽሯል ።

፪/ በወለድ አግድ የከተማን የመኖሪያ ቤት ፤ ወይም የመሥሪያ ቤት የያዘ አበዳሪ በቤቱ በመጠቀም ወይም በማከራየት ያገኘው ጥቅም ከአበደረው ገንዘብ ጋር ተመጣጣኝ ወይም የሚበልጥ ሆኖ ከተገኘ ፤ ተበዳሪው ከዕዳው ነፃ ይሆናል ።

፫/ በወለድ አግድ የተያዘ የመኖሪያ ፤ ወይም የመሥሪያ ቤት በአንቀጽ ፲፮ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) መሠረት ለባለቤቱ የሚመለስ ወይም በትርፍ ቤትነት በመንግሥት የሚወረስም ቢሆን አበዳሪው ካበደረው ገንዘብ ተመጣጣኝ ጥቅም ያላገኘ ከሆነ ቀሪውን ሒሳብ ከተበዳሪው የማስከፈል መብቱ የተጠበቀ ነው ።

16. *Right to Repossess Own House*

1/ Where a person has his own urban house but resides under any arrangement in an urban house that of another, such person may repossess his house. Likewise, a person who owns more than one urban house may repossess the house of his choice. However, where the Ministry ascertains that the house is necessary for business purposes or that the house is capable of accommodating more than one family, this sub-article shall have no application and such house shall be Government property.

2/ Any person who has one or more business houses held in antichresis by another may, where he has no other business house, repossess the house of his choice upon producing a licence for the business he wishes to undertake. However, where the Ministry ascertains that such house cannot be used as a business house, this sub-article shall have no application and such house shall be Government property.

3/ Any person or family shall have the right to evict his or its co-dweller by giving the notice mentioned in sub-article (4) of this Article.

4/ Any person who decides to exercise his right under sub-article (1) or (2) of this Article shall give 6 months' notice to the person occupying the house.

5/ Subject to Article (20) (4) and Article 21 (2), (3), and (4), the lessee shall continue to pay rent to the Government or to the co-operative society of urban dwellers pending the handing over of the house.

6/ Where a person or family leaves for business purposes the urban area of his or its habitual residence and if such person or family has a dwelling house of his or its own in such urban area, the Ministry or the co-operative society of urban dwellers shall, where the person or family so requests, provide such person or family with a comparable dwelling house or commensurate housing allowance. The Ministry, shall take over the administration of the dwelling house of said person or family and upon the return of the person or family to the place of his or its habitual residence hand it over to its owner.

17. *Houses Held in Antichresis*

1/ Upon the effective date of this Proclamation, all contracts of antichresis involving urban houses are hereby abolished.

2/ Where the lender in a contract of antichresis has, by the use to which he had put the house or by the rent which he has received, obtained an amount equivalent to or more than the amount of the loan, the borrower shall be free from his debt.

3/ Where the lender in a contract of antichresis involving an urban dwelling or business house which is revertible to the owner or is liable to be Government property under sub-article (1) or (2) of Article 16 has not obtained from such house an amount or service equivalent to or more than the amount of the loan, such lender shall be entitled to claim the difference from the borrower.

፲፰፤ ለተወረሱ ት[illegible] ቤቶች ካሣ ስለመክፈል ፤

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት ለተወረሱ ቤቶች መንግሥት ተገቢውን ካሣ ይከፍላል ።

፪/ ከነሐሴ ፩ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. በኋላ ላለው ጊዜ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት የተከፈለ ኪራይ ፤ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለተወረሱ ቤቶች ከሚከፈል ካሣ ይቀነሳል ።

፫/ በአንቀጽ ፲፬ በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለተወረሱ ቤቶች ካሣ ወይም ኪሣራ አይከፈልም ።

፲፱፤ የከተማ ቤት ለሕዝብ አገልግሎት ስለማስለቀቅ ፤

በግለሰብ ፤ በቤተሰብ ወይም በድርጅት የተያዘ የከተማ ቤት መንግሥት ለሕዝብ አገልግሎት ለማዋል የሚያስፈልገው ሲሆን ካሣ ከፍሎ ቤቱን ሊወስድ ይችላል ።

ምዕራፍ ፬

ስለ ኪራይ

፳፤ ስለቤት ኪራይ ፤

፩/ ከነሐሴ ፩ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. ጀምሮ ሚኒስቴሩ ወይም የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበሮች ካልሆኑ በስተቀር ማናቸውም ቤተሰብ ፤ ግለሰብ ወይም ድርጅት ከከተማ ቤትና ከከተማ ቦታ የኪራይ ገቢ ሊያገኝ አይችልም ።

፪/ ከነሐሴ ፩ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. ጀምሮ በአከራይና በተከራይ መካከል የነበረው ግንኙነት ተቋርጧል ። ሆኖም የተከራዩ ግንኙነት በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፭) መሠረት ከሚኒስቴሩ ወይም ከከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር ጋር ይቀጥላል ።

፫/ ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የተደረገ ማንኛውም የኪራይ ውል ጊዜው ከታኅሣሥ ፳፪ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ. ም. በፊት የሚያልቅ ከሆነ ሚኒስቴሩ ወይም የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር ከተከራዩ ጋር አዲስ ድርድር ለማድረግ ይችላል ።

፬/ ኪራይን የሚወስን ደንብ እስከወጣ ድረስ ኪራያቸው ከ፫፻ ብር የማይበልጥ የከተማ መኖሪያ ቤቶችና መሥሪያ ቤቶች ኪራይ ከነሐሴ ፩ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. ጀምሮ በሚከተለው መጠን ተቀንሷል ።

ሀ/ በወር እስከ ፳፭ ብር ለሚከፍሉ ፶ በመቶ ፤

ለ/ በወር ከ፳፭ ብር በላይ እስከ ፶ ብር ለሚከፍሉ ፵ በመቶ

ሐ/ በወር ከ፶ ብር በላይ እስከ ፻ ብር ለሚከፍሉ ፴ በመቶ

መ/ በወር ከ፻ ብር በላይ እስከ ፻፶ ብር ለሚከፍሉ ፳፭ በመቶ ፤

ሠ/ በወር ከ፻፶ ብር በላይ እስከ ፪፻ ብር ለሚከፍሉ ፳ በመቶ ፤

ረ/ በወር ከ፪፻ ብር በላይእስከ ፫፻ ብር ለሚከፍሉ ፲፭ በመቶ ፤

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) በተመለከተው መሠረት በወር ፤

ሀ/ እስከ ፻ ብር የሚከራዩ የከተማ መኖሪያ ቤቶች ወይም መሥሪያ ቤቶች ኪራይ የሚሰበስበውና ጠቅላላ የቤቶቹ አስተዳደር የሚካሔደው በከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር ኃላፊነት ነው።

18. *Payment of Compensation for Extra Houses*

1/ The Government shall pay fair compensation in[…] pect of houses transferred to Government owne[…] under this Proclamation.

2/ Where advance rent for the period after Nehas[…] 1967 has been paid before the effective dat[…] this Proclamation, the amount of such rent sha[…] substracted from the compensation payable under […] article (1) of this Article.

3/ No compensation or damage shall be due in re[…] of houses transferred to Government ownership u[…] Article 14 (1).

19. *Expropriation of Houses*

The Government may, by paying compensation, exprop[…] for public purpose an urban house held by any pe[…] family or organization.

CHAPTER IV

RENT

20. *House Rent*

1/ No person, family or organization except the Mini[…] or co-operate societies of urban dwellers may, a[…] the effective date of this Proclamtion, obtain inc[…] from urban land or house rent.

2/ The relationship between lessor and lessee is he[…] abolished as of the effective date of this Proclama[…] However, the lessee — lessor relationship shall c[…] tinue with the Ministry or with the co-operative […] ciety of urban dwellers in accordance with sub-ar[…] (5) of this Article.

3/ Where a contract of lease made before the effe[…] date of this Proclamation expires before Tahsas[…] 1968, the Ministry or the co-operative society o[…] ban dwellers may renegotiate the lease with the le[…]

4/ Until a rent control regulation is issued the ren[…] urban dwelling and business houses not excee[…] $ 300 shall as of Nehasie 1, 1967, be red[…] by the following percentages:-

a) monthly rent of upto $ 25 ....50%

b) monthly rent of above $ 25 but not exceeding $ 50 ....40%

c) monthly rent of above $ 50 but not exceeding $ 100 ....30%

d) monthly rent of above $ 100 but not exceeding $ 150 ....25%

e) monthly rent of above $ 150 but not exceeding $ 200 ....20%

f) monthly rent of above $ 200 but not exceeding $ 300 ....15%

5/ The rent and the administration of urban dwelling[…] business houses which under sub-article (4) of […] Article rent at the rate of:

a) upto $ 100 per month shall be the responsib[…] of co-operative societies of urban dwellers.

SAMUEL GIRMA

ለ/ ከ፩፻ ብር በላይ የሚከራዩ የከተማ መኖሪያ ቤቶች ወይም የሥራ ቤቶች ኪራይ የሚሰበሰበውና ጠቅላላ የቤቶቹ አስተዳደር የሚካሔደው በሚኒስቴሩ ኃላፊነት ነው ።

፮/ በከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር የሚሰበሰበው ኪራይ የአካባቢውን ነዋሪዎች በሚጠቅም ተግባር ላይ ይውላል ።

፯/ ሚኒስቴሩ የሚሰበስበው ኪራይ ለጠቅላላ የከተማ ነዋሪዎች ኑሮ ማሻሻያ ና ለከተማ ዕድገት ይውላል ።

፳፩ ፤ ልዩ አስተያየት የሚደረግላቸው ድርጅቶችና ግለሰቦች ፤

፩/ የከተማ ቤት የተወሰረበት የሃይማኖት ፤ የትምህርት ፤ የጤና ጥበቃ ወይም ተመሳሳይ አገልግሎት ለሚሰጥ ድርጅት መንግሥት አስፈላጊነቱን እያጠና ለመተዳደሪያ የሚሆን በጀት ይመድብለታል ።

፪/ ትርፍ ቤት የተወረሰበት ቤተሰብ ወይም ግለሰብ ከቤት ኪራይ በስተቀር ለመኖሪያ የሚሆነው ሌላ ገቢ የሌለው መሆኑ በሚኒስቴሩ ከተረጋገጠ በመሥራት ገቢ እስኪያገኝ ድረስ ሚኒስቴሩ ወይም የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር በየወሩ ለመተዳደሪያ እስከ ፪፻፶ (ሁለት መቶ ሃምሳ) ብር ይከፍለዋል።

፫/ የከተማ ቤት የተወረሰበት ለአካለ መጠን ያልደረሰ ሰው ራሱ ወይም ወላጆቹ ከቤቱ ኪራይ በስተቀር ለመተዳደሪያ ሌላ ገቢ እንደሌላቸው ሚኒስቴሩ ካረጋገጠ በመሥራት ገቢ እስኪያገኝ ወይም አካለ መጠን እስከ ደረሰ ድረስ ሚኒስቴሩ ወይም የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር በየወሩ ለመተዳደሪያ እስከ ፪፻፶ (ሁለት መቶ ሃምሳ) ብር ድረስ ይከፍለዋል ።

፬/ ትርፍ ቤት የተወረሰበት ቤተሰብ ወይም ግለሰብ በመሥራት ፤ በጡረታ ወይም በተመሳሳይ ሁኔታ የሚያገኘው የወር የተጣራ ገቢው ከ፪፻ (ሁለት መቶ) ብር የማይበልጥ መሆኑ በሚኒስቴሩ ከተረጋገጠ ሚኒስቴሩ ወይም የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር በወር እስከ ፩፻ (አንድ መቶ) ብር ድረስ ይከፍላል ።

፭/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) ፤ (፪) ፤ (፫) ፤ እና (፬) መሠረት ሚኒስቴሩ ወይም የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር የሚያደርገው ክፍያ በኃላፊነቱ ከሚሰበስበው ከኪራዩ ገቢ ሆኖ ለቤተሰብ ፤ ለግለሰብ ወይም ድርጅት የሚከፈለውም ገንዘብ ከኪራይ ገቢ ከሚገኘው መጠን ሊበልጥ አይችልም ።

፮/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚደረግ ክፍያ ለከተማ ቤት ከሚከፈለው ካሣ ተቀናሽ ይሆናል ። ጠቅላላ ክፍያው ለቤቱ ከሚሰጠው ካሣ ሊበልጥ አይችልም ።

፯/ ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በቅድሚያ የተወሰደ ኪራይ ካለ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) ፤ (፪) ፤ (፫) ፤ እና (፬) መሠረት ከሚደረገው ክፍያ ላይ ተቀናሽ ይሆናል ።

b) above $ 100 per month shall be the responsibility of the Ministry.

6/ The rents collected by co-operative societies of urban dwellers shall be utilized for purposes beneficial to the dwellers.

7/ The rents collected by the Ministry shall be utilized for the improvement of the lives of all urban dwellers and of urban areas.

21. *Organizations and Families under Special Consideration*

1/ The Government shall, where it considers it necessary, Provide budgets to religious, educational or health or similar organizations whose urban house has been transferred to the Government.

2/ Where the Ministry ascertains that a person or family has no income other than the rent he or it used to collect from his or its extra house which has been transferred to the Government under this Proclamation, the Ministry or the co-perative society of urban dwellers shall, until the person or family earns income by working, pay such person or family an amount upto Two Hundred and Fifty (250) Dollars per month.

3/ Where the Ministry ascertains that a minor or his parent has no income other than the rent which the minor used to collect from his extra house which has been transferred to the Government under this Proclamation, the Ministry or the co-operative society of urban dwellers shall, until the minor attains majority or earns income by working, pay such person an amount upto Two Hundred and Fifty (250) Dollars per month.

4/ Where the Ministry ascertains that the monthly net income from work, pension and from other sources of a person or family whose extra house has been transferred to the Government under this Proclamation does not exceed Two Hundred (200) Dollars the Ministry or the co-operative society of urban dwellers shall pay him or it an amount up to One Hundred (100) Dollars per month.

5/ Payments under sub-articles (1), (2), (3) and (4) of this Article shall be made by the Ministry and the co-operative society of urban dwellers from the rent which is collected under their respective responsibilities. The payment to which a person, family or an organization is entitled under this Article shall not exceed the amount of income from rent.

6/ Payments made under this Article shall be deducted from the compensation to be paid by the Government for extra houses taken by it. The total of payments made under this Article, may not exceed the amount of compensation.

7/ Where advance rent has been collected before the effective date of this Proclamation, such rent shall be deducted from the amount payable under sub-articles (1), (2), (3) and (4) of this Article.

ምዕራፍ ፭
የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበሮች ፤

፳፪ ፤ የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበሮች ስለማቋቋም፤

ሚኒስቴሩ በሚወስነው የከተማ ክልል ውስጥ የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበሮች ይቋቋማሉ ።

፳፫ ፤ የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር አባሎች ፤

ማንኛውም የከተማ ነዋሪ የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር አባል ለመሆን ይችላል ። ሆኖም ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት አከራይ የነበረ ማንኛውም ሰው በመጀመሪያው አንድ ዓመት ጊዜ ብቻ የማኅበሩን ሹማምንት የመምረጥ መብት ሊኖረው አይችልም ። እንዲሁም የማኅበሩ የፍርድ ሸንጎ ፤ የማኅበሩ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ፤ ወይም የሕዝብ ደኅንነት ጥበቃ ኮሚቴ አባል ለመሆን አይችልም ።

፳፬ ፤ የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር ተግባር ፤

የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር የሚከተለው ተግባር ይኖረዋል ፤

፩/ ስለከተማ መሬት አጠቃቀምና ስለቤት አሠራር ሚኒስቴሩ የሚሰጠውን መመሪያ እየተከተለ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል ።

፪/ ሦስት አባላት ያሉት የፍርድ ሸንጎ ያቋቁማል ።

፫/ ከመንግሥት ጋር በመተባበር ለአካባቢው የሚያስፈልጉትን የትምህርት ፤ የጤና ፤ የገበያ ፤ የመንገድ ሥራና የመሳሰሉትን አገልግሎቶች ያቋቁማል ።

፬/ ሚኒስቴሩ በሚያዘጋጅለት ደረሰኞች መሠረት በወር እስከ ፻ ብር የሚከራይ የከተማ ቤትና ቦታ ኪራይ ይሰበስባል ። የቤቶቹንም ጠቅላላ አስተዳደርና ጥገና ያካሒዳል ።

፭/ ማኅበሩ የሰበሰበውን ኪራይ በሕዝባዊ የመኖሪያ ቤትና የቁጠባ ባንክ ሚኒስቴሩ በሚከፍትለት ሒሳብ ውስጥ ያስቀምጣል ።

፮/ የኅብረት ሥራው ማኅበር በተቋቋመበት የከተማ ክልል ውስጥ የሚገኙትን ማናቸውንም የሕዝብና የመንግሥት ንብረት መጠበቅና በተለይም ከመንግሥት ድርጅቶች ጋር በመተባበር የአካባቢው ሕዝብ ደኅንነትና ሕይወት በተሟላ ሁኔታ እንዲረጋገጥና እንዲከበር ያደርጋል ። ማኅበሩ ይህንኑ ሥራ ለማስፈጸም የሕዝብ ደኅንነት ጥበቃ ኮሚቴ ያቋቁማል ።

፯/ ማኅበሩ በሚሰበስበው ኪራይና ከመንግሥት በሚያገኘው ድጎማ ሚኒስቴሩ በየጊዜው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ለአካባቢው ሕዝብ የቁጠባ ቤት እንዲሠራለትና የኑሮውንም ሁኔታ የሚያሻሽሉ ተግባሮች እንዲደረጉ ያደርጋል ።

፰/ ማኅበሩ ያዋጁን መንፈስ የተከተለ የራሱን የውስጥ ደንብ ያወጣል ። በሚኒስትሩም ሲጸድቅ ሥራ ላይ ይውላል ።

፳፭ ፤ የከፍተኛ ከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር ስለማቋቋም ፤

፩/ እንደ ከተማው ስፋትና እንደሕዝቡ ብዛት የከተማ ነዋሪዎች ማኅበር ተወካዮች የሚገኙበት ከፍተኛ የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር ይቋቋማል ።

CHAPTER V
CO-OPERATIVE SOCIETIES OF URBAN DWELLER

22. *Establishment of Co-operative Societies of Urban Dwe*

There shall be established a co-operative society of u dwellers in each unit of urban area as determined by Ministry.

23. *Membership of Co-operative Society of Urban Dweller*

Any urban dweller may become a member of a co-op tive society of urban dwellers. However, a person who a lessor before the effective date of this Proclamation not have the right for the first one year period to elec ficials of the co-operative society of urban dwellers an be a member of the judicial tribunal, executive commi or public welfare committee of the society.

24 *Functions of Co-operative Societies of Urban Dwellers*

The functions of a co-operative society of urban dwel shall be the following:

1/ to follow and execute land use and building direct to be issued by the Ministry;

2/ establish a judicial tribunal composed of three m bers;

3/ to set up, with the co-operation of the Governm educational, health, market, road and similar serv necessary for the area;

4/ to collect urban land and house rent amounting u $ 100 per month per house or per piece of land u the receipt form issued by the Ministry and to un take the administration and repairs of such houses

5/ to deposit the rents it collect with a Peoples' Hou and Savings Bank in an account opened by the Mi try;

6/ to preserve, by establishing a public welfare com tee, all public and Government property within area and in particular to ensure, with the co-opera of Government authorities, the protection of the w fare and lives of the people in the area;

7/ to expend, in accordance with directives issued by Ministry, the rents it collects and the subsidy it obt from the Government for the building of econom houses and the improvement of the quality of life urban dwellers in the area;

8/ to draw up its internal regulations consistent with requirements of this Proclamation, which shall be fective upon the approval of the Minister.

25. *Establishment of Higher Co-operative Societies of Urb Dwellers.*

1/ There shall be established, depending on the size a population of the urban area, a higher co-operat society of urban dwellers.

SAMUEL GIRMA

፪/ ከፍተኛ የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር የሚከተለው ተግባር ይኖረዋል ፤—

ሀ/ በአንቀጽ ፳፬ በንዑስ አንቀጽ (፩) ፤ (፫) ፤ (፬) ፤ (፭) (፮ ፤ ፯) እና (፰) የተጠቀሱትን የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር ተግባሮች ያስተባብራል ፤

ለ/ በከፍተኛ የኅብረት ሥራ ማኅበር ክልል ውስጥ የሚገኙ ማኅበሮች በተቻለ መጠን የተመጣጠነ ይዞታ እንዲኖራቸው ለማድረግ ይዞታን በማሸጋሸግ ረገድ ሚኒስቴሩን ይረዳል ፤

ሐ/ ማንኛውም የከተማ ቦታ የሌለው ቤተሰብ ፤ ግለ ሰብ ወይም ድርጅት ለመኖሪያ ወይም ለመሥሪያ ቤት መሥሪያ የሚያውለው ቦታ ሚኒስቴሩ እንዲሰጠው ሲያመለክት ከሚኒስቴሩ ጋር በመመካከርና በመተባበር በአስፈላጊው ሁሉ ይረዳል ፤

መ/ ሦስት አባላት ያሉበት ከፍተኛ የፍርድ ሸንጎ ያቋቁማል ።

፳፮ ፤ የአጠቃላይ የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር ስለማቋቋም ፤

፩/ እንደ ከተማው ስፋትና እንደሕዝቡ ብዛት የያንዳንዱ ከፍተኛ ያከተማ ነዋሪዎች ማኅበር ተወካዮች የሚገኙ በት አጠቃላይ የከተማ ነዋሪዎች ማኅበር ይቋቋማል።

፪/ የአጠቃላይ የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር የሚከተለው ተግባር ይኖረዋል ።

ሀ/ የከፍተኛ የከተማ ነዋሪዎችን የኅብረት ሥራ ማኅበር ተግባር ያስተባብራል ፤

ለ/ ሦስት አባላት ያሉበት አጠቃላይ የፍርድ ሸንጎ ይቋቋማል ።

፳፯ ፤ ስለፍርድ ሸንጎዎች ፤

፩/ በአንቀጽ ፳፬ በንዑስ አንቀጽ (፪) የሚቋቋመው የከተማ ነዋሪዎች የፍርድ ሸንጎ ፤

ሀ/ በነዋሪዎች መካከል የሚነሱትን የከተማ ቦታና ቤት ነክ ክርክሮች በመጀመሪያ ደረጃ አይቶ ለመ ወሰን ሥልጣን አለው ።

ለ/ የወንጀል ክስና እንዲሁም በማኅበሩና በነዋሪዎች መካከል የሚነሣውን ክርክር ለማየት ሥልጣን የለ ውም ።

፪/ በአንቀጽ ፳፭ ንዑስ አንቀጽ (፪) (መ) የሚቋቋመው ከፍተኛ የከተማ ነዋሪዎች የፍርድ ሸንጎ ፤

ሀ/ በከተማ ነዋሪዎች ፍርድ ሸንጎ የተወሰነውን ክር ክር በይግባኝ አይቶ ይወስናል ። በይግባኝ አይቶ የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል ።

ለ/ በከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበሮች መካ ከል ፤ እንዲሁም በከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበርና በነዋሪዎች መካከል የሚነሣውን የከተማ ቦታና ቤት ነክ ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ አይቶ ለመወሰን ሥልጣን አለው ።

ሐ/ የወንጀል ክስ ለማየት ሥልጣን የለውም ።

፫/ በአንቀጽ ፳፮ በንዑስ አንቀጽ (፪) (ለ) የሚቋቋመው አጠቃላይ የከተማ ነዋሪዎች የፍርድ ሸንጎ ፤

ሀ/ በከፍተኛ የከተማ ነዋሪዎች የፍርድ ሸንጎ በመጀ መሪያ ደረጃ የተወሰነውን ክርክር በይግባኝ አይቶ ይወስናል ። በይግባኝ አይቶ የሰጠው ውሳኔ የመ ጨረሻ ይሆናል ።

2/ The functions of a higher co-operative society of urban dwellers shall be:

a) to co-ordinate the functions of co-operative societies of urban dwellers mentioned in Article 24, (1), (3), (4), (5), (6), (7) and (8);

b) to assist the Ministry in changing the boundaries of areas so that co-operative societies of urban dwellers within the jurisdiction of the higher co-operative society have as far as possible equal holdings;

c) to co-operate with and assist the Ministry in processing applications submitted to the Ministry by any person who or family or organization which has no urban land and seeks to obtain such land for dwelling or business purposes;

d) establish a higher judicial tribunal composed of three members.

26. *Establishment of Central Co-operative Societies of Urban Dwellers*

1/ There shall be established, depending on the size and population of the urban area, a central co-perative society of urban dwellers which shall be composed of delegates of higher co-operative societies of urban dwellers.

2/ The functions of central co-operative societies of urban dwellers shall be:

a) to co-ordinate the functions of higher co-operative societies of urban dwellers; and

b) to establish a central judicial tribunal composed of three members.

27. *Judicial Tribunals*

1/ The judicial tribunal to be established under Article 24 (2) shall,

a) have first instance jurisdiction to hear and decide disputes involving urban land or house arising between urban dwellers.

b) not have jurisdiction to hear criminal cases and disputes arising between the co-operative society and urban dwellers.

2/ The higher judicial tribunal to be established under Article 25 (2) (d) shall:

a) hear and decide on appeals from judicial tribunals and such decision shall be final.

b) have first instance jurisdiction to hear and decide disputes involving urban land or house arising between co-operative societies of urban dwellers, and between co-operative societies of urban dwellers and urban dwellers.

c) not have jurisdiction to hear criminal cases.

3/ The central judicial tribunal to be established under Article 26 (2) (b) shall:

a) hear and decide on appeals from decisions of a higher judicial tribunal in its first instance jurisdiction and such appellate decision shall be final.

SAMUEL GIRMA

ለ/ በከፍተኛ የከተማ ነዋሪዎች ማኅበሮች መካከል የሚነሣውን የከተማ ቦታና ቤት ነክ ክርክር፤በመጀመሪያ ደረጃ ለመወሰን ሥልጣን አለው ። በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኙ በሚኒስትሩ ይታያል ። የሚኒስትሩ ውሳኔም የመጨረሻ ይሆናል ።

ሐ/ የወንጀል ክስ ለማየት ሥልጣን የለውም ።

፬/ በማንኛውም ከተማ ከፍተኛ የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር ወይም አጠቃላይ የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር ከሌለ የፍርድ ሸንጎ እስከተቋቋመ ድረስ ሚኒስትሩ የሚወክለው ሰው ወይም ድርጅት እንደከፍተኛ ወይም አጠቃላይ የፍርድ ሸንጎ ሆኖ ለመሥራት ሥልጣን ይኖረዋል ።

፳፰ ፤ ስለፍርድ ሸንጎዎች ሥነ ሥርዓት ፤

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚቋቋሙ የፍርድ ሸንጎዎች ሚኒስትሩ የሚያወጣውን የሥነ ሥርዓት መመሪያ በመከተል ሥራቸውን ያከናውናሉ ።

፪/ የፍርድ ሸንጎዎች የሚሰጡት ውሳኔ ወይም ትእዛዝ በይግባኝ ካልታገደ በስተቀር ከ፲፭ ቀን በኋላ ተፈጻሚነት ይኖረዋል ።

፫/ የፍርድ ሸንጎዎች በሚሰጡት ውሳኔ ወይም ትእዛዝ ላይ ይግባኝ የሚቀርበው በ፲፭ ቀን ጊዜ ውስጥ ነው።

፬/ የፍርድ ሸንጎዎች የሚሰጡት ውሳኔ ወይም ትእዛዝ በደረጃው ባሉት ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አማካይነት በሥራ ላይ ይውላል ። የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው የተሰጠውን ውሳኔ ወይም ትእዛዝ ከሥራ ላይ ለማዋል ያልቻለ እንደሆነ የፍርድ ሸንጎው ፖሊስን በቀጥታ በማዘዝ ውሳኔውን ወይም ትእዛዙን ያስፈጽማል ።

፳፱ ፤ የፍርድ ሸንጎውን ስለመድፈር ፤

የፍርድ ሸንጎው ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ሥራውን ለሚያሰናክል ፤ የስድብ ፤ የዛቻ ፤ የፌዝና ተመሳሳይ የሁከት አድራጎት በፈጸመ ማንም ሰው ላይ እስከ ሠላሳ ቀን የሚደርስ እሥራት ወይም እስከ ፪፻፶ (ሁለት መቶ ሃምሳ) ብር ለመድረስ በሚችል ገንዘብ መቀጮ በራሱ ሥልጣን ክስ ጠሮ ሳያደርግ ወዲያውኑ መቅጣት ይችላል።

፴ ፤ ስለፍርድ ሸንጎዎች ሥልጣን ማጣራት ፤

ማንኛውም ሰው በፍርድ ሸንጎ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወሰንበት ጉዳይ የይግባኝ መብቱን በሸንጎዎቹ በየደረጃው ከጨረሰ በኋላ ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ለማቅረብ አይችልም ። ሆኖም በፍርድ ሸንጎ የተሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ወይም ትእዛዝ ከፍርድ ሸንጎው ሥልጣን ውጭ መሆኑን ሚኒስትሩ በሚቀርብለት ማመልከቻ መሠረት ካመነበት ጉዳዩን አጣርቶ በዚህ አዋጅ መሠረት ውሳኔ ሊሰጥበት ይችላል ። የሚኒስትሩ ውሳኔም የመጨረሻ ይሆናል ።

ምዕራፍ ፮

የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር

፴፩ ፤ አዋጁን የማስፈጸም ሥልጣን ፤

ሚኒስቴሩ ይህ አዋጅ የሚደነግገውን ሁሉ ለማስፈጸም ሥልጣን ይኖረዋል ።

b) have first instance jurisdiction to hear and disputes involving urban land or house between higher co-operative societies of dwellers, provided that such decision sh appealable to the Minister whose decisio be final.

c) not have jurisdiction to hear criminal case

4/ In urban areas which do not have higher and co-operative societies of urban dwellers, perso organizations appointed by the Minister sh as higher and central judicial tribunals until su as they are replaced by such tribunals.

28. *Procedure of Judicial Tribunals*

1/ Judicial tribunals established under this Procla shall follow the rules of procedure issued Minister.

2/ The decision of a judicial tribunal shall be fifteen days after the date of decision unless on appeal.

3/ An appeal from a decision or order of a judici nal shall be made within fifteen days of the decision.

4/ The decision or order of a judicial tribunal executed by the executive committee of the ponding co-operative society. Where the e committee is unable to execute the judicial or order, the judicial tribunal shall execute sa sion or order by directly ordering the Police.

29. *Contempt of Judicial Tribunal*

Where a person, in the course of a judicial tribu ceeding, insults, threatens, holds up to ridicule or manner disturbs the tribunal, the tribunal may su punish such person with imprisonment upto 30 day upto Two Hundred Fifty (250) Dollars.

30. *Ultra vires Decisions of Judicial Tribunals*

No person who has exhausted his right of appe judicial tribunals may lodge an appeal to the courts of law. However, where the Minister from an application submitted to him that the ju bunal's decision is *ultra vires*, the Minister shall re case and decide it under this Proclamation. The of the Ministe: shall not be subject to appeal.

CHAPTER VI

POWERS AND DUTIES OF THE MINISTRY

31. *Implementation of this Proclamation*

The Ministry shall have the power to implemen visions of this Proclamation.

፴፪ ፤ የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር ስለማቋቋም፤

፩/ ሚኒስቴሩ ከአገር አስተዳደር ሚኒስቴርና አግባብ ካላቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር ለከተሞች ልማትና ለነዋሪዎች በሚስማማ ሁኔታ በዚህ አዋጅ መሠረት የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር በየደረጃው እንዲቋቋም ያደርጋል ።

፪/ ሚኒስትሩ የከተማ ነዋሪዎችን የኅብረት ሥራ ማኅበር በምክርና በሌላም ልዩ/ልዩ መንገድ የሚረዳ ቢያንስ በየከፍተኛ የከተማ ነዋሪዎች ማኅበር አንድ ወኪል ይመድባል ።

፴፫ ፤ አዋጁን ለሕዝብ በይፋ ስለማሳወቅ ፤

፩/ ሚኒስትሩ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችና ዓላማ በማንኛውም የመገናኛ ዘዴ ለከተማ ሕዝብ ያስረዳል ።

፪/ በተለይም ሚኒስትሩ ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን ጀምሮ ወዲያውኑ በከተማ ባለርስትና ጭሰኛ ፤ በወለድ አግድ አያስሻርና በወለድ አግድ ያዥ መካከል ያለውን ግንኙነት መቋረጡንና የተከራዩ ግንኙነት ከሚኒስቴሩ ወይም ከከተማ የኅብረት ሥራ ማኅበር ጋር መሆኑን ይገልጣል ፤ የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበሮች የሚቋቋሙበትንም ሁኔታ ያስረዳል ።

፫/ የሚኒስትሩ ወኪል የከተማ ነዋሪዎችን በመሰብሰብና የዚህን አዋጅ መንፈስና ዓላማ በመግለጽ ማኅበሩ እንዲቋቋም ያደርጋል ።

፴፬ ፤ ሚኒስቴሩ በፍርድ ሸንጎ ለመካፈል ያለው ጊዜያዊ ሥልጣን ፤

፩/ የሚኒስቴሩ ወኪሎች ፤ የከተማ ነዋሪዎች የፍርድ ሸንጎዎች ተደራጅተው ሥራ ለማካሔድ እስከቻሉ ድረስ በሸንጎው ውስጥ በሊቀ መንበርነት ይሠራሉ ። ሆኖም ማንኛውም ወኪል በመጀመሪያ ደረጃ ያየውን ክርክር በይግባኝ ደረጃ መልሶ ለማየት አይችልም።

፪/ የሚኒስቴሩ ወኪሎች የፍርድ ሸንጎ ጽሕፈት ቤቶች አቋቁመው በመዝገብ አያያዝ ረገድ ያለውን ሥራ በማደራጀት ይረዳሉ ።

፴፭ ፤ መዝገብ ስለማቋቋምና ስለከተማ ክልሎች መወሰን ፤

፩/ ሚኒስቴሩ የከተማ ነዋሪዎች ዝርዝርና የቤቶችን ብዛትና ሁኔታ የሚያሳይ መዝገብ በየደረጃው ያቋቁማል።

፪/ ሚኒስትሩ ከአገር አስተዳደር ሚኒስትርና አግባብ ካላቸው ሌሎች የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር የከተማ ክልል ወሰኖችን ለማስፋትና ለማጥበብ ወይም ለመለየት ሥልጣን አለው ።

፴፮ ፤ የከተማ ነዋሪዎችን የኑሮ ሁኔታ ስለማሻሻል ፤

፩/ ሚኒስትሩ ከገንዘብ ሚኒስትር ፤ ከፕላንና ልማት ኮሚሽን ፤ ከብሔራዊ ባንክና ከሌሎችም አግባብ ካላቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር የከተማ ነዋሪዎች ብድር አግኝተው የራሳቸውን የመኖሪያ ቤት ለመሥራት ወይም ለመግዛት እንዲችሉ ይረዳል ።

፪/ መንግሥት በጠቅላላው ስለከተሞች ዕድገት በሚያወጣው ዕቅድና መምሪያ መሠረት ሚኒስቴሩ የሚሰበስበው ኪራይ ለከተማ ነዋሪዎች አገልግሎት ይውላል።

32. *Establishment of Co-operative Societies of Urban Dwellers*

1/ The Ministry shall, in co-operation with the Ministry of Interior and other concerned Public Authorities, establish at all levels co-operative societies of urban dwellers under conditions which facilitate urban development and conform with the needs of urban dwellers.

2/ The Minister shall, at least at the level of higher co-operative society of urban dwellers, designate one person who shall advise and otherwise assist co-operative societies of urban dwellers.

33. *Publicizing of the Proclamation*

1/ The Minister shall notify and explain to the public the provisions and purposes of this Proclamation through the mass media.

2/ In particular, the Minister shall notify the public of the termination of the relationship between lessor and lessee and of the contract of antichresis, and of the continuation of the lessee — lessor relationship with the Ministry or the co-operative society of urban dwellers and shall explain the conditions under which such societies shall be established.

3/ The person designated by the Minister shall help in the establishment of co-operative societies of urban dwellers by calling assemblies of urban dwellers and explaining the purposes and intentions of this Proclamation.

34. *Temporary Power of the Ministry to Preside over Judicial Tribunals*

1/ The persons designated by the Ministry shall preside over the judicial tribunals until such time as the judicial tribunals are well organized and fully operational. However, no such person who has presided over a case heard at a lower judicial tribunal may do the same at a higher level.

2/ The said persons shall establish the offices of judicial tribunals and shall assist in organizing the records of the offices.

35. *Establishment of Registers and Delimitation of Urban Boundaries*

1/ The Ministry shall establish at all levels registers showing the list of urban dwellers, number and condition of houses.

2/ The Minister shall have the power to widen, narrow and demarcate urban boundaries in co-operation with the Minister of Interior and other concerned Public Authorities.

36. *Improving the Lives of Urban Dwellers*

1/ The Minister shall, in co-operation with the Minister of Finance, Planning Commission, National Bank and other concerned Public Authorities, assist urban dwellers to procure loans for the purpose of building or buying their own dwelling houses.

2/ The rents collected by the Ministry shall, in accordance with comprehensive urban development plans and directives issued by the Government, be utilized for providing services to urban dwellers.

፫/ ሚኒስቴሩ በከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር የሚሰበሰበውን ኪራይ መንግሥት በጠቅላላው ስለከተማዎች ዕድገት በሚያወጣው ዕቅድና መመሪያ መሠረት ለአካባቢው የኅብረት ሥራ ማኅበር ማስፋፊያ አገልግሎት እንዲውል ያደርጋል ።

፬/ ሚኒስቴሩ የከተማ ቦታዎችንና የመንግሥትን የከተማ ቤቶች በበላይነት ያስተዳድራል ።

፭/ ሚኒስቴሩ ለከተሞች ፕላን በማውጣት የቁጠባ ቤቶችን ይሠራል ፤ ለከተማ ነዋሪዎች አስፈላጊ የሆኑትን አገልግሎቶችንም ይሰጣል ።

፮/ ሚኒስቴሩ ከአገር አስተዳደር ሚኒስቴርና ከከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበሮች ጋር በመተባበር ቦታ ለሌለው የከተማ ነዋሪ ሕዝብ ቤት መሥሪያ የሚሆነውን ቦታ እንዲሰጥ ያደርጋል ።

፯/ ሚኒስቴሩ የከተማ ቤቶችን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ደረጃ (እስታንዳርድ) እያወጣ በሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል ።

፰/ ሚኒስትሩ ወይም የሚወክለው ሰው ወይም ድርጅት ይህ አዋጅ በጸናበት ቀን ያልተከራዩ ቤቶችን ኪራይ ይወስናል ።

፴፯ ፤ መረጃ የመጠየቅ ሥልጣን ፤

የሚኒስቴሩ ወኪል ለሥራው አስፈላጊ የሆኑትን የውል ሰነዶችና ሌሎችም መረጃዎች ከሌሎች የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ፤ ከግል የንግድና የኅብረት ሥራ ድርጅቶችና ከግለሰቦች ጠይቆ ለማግኘት ሥልጣን አለው ።

ምዕራፍ ፯

ጠቅላላ ውሳኔዎች

፴፰ ፤ ስለከተማ ማኅበሮች የሕግ ሰውነት ፤

በዚህ አዋጅ መሠረት በየደረጃው የሚቋቋሙት የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበሮች የየራሳቸው የሕግ ሰውነት ይኖራቸዋል ።

፴፱ ፤ ስለመደበኛ ፍርድ ቤት ሥልጣን ፤

በአንቀጽ ፲፯ በንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ፤ እንዲሁም ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን በፊት ቀርቦ በመደበኛ ፍርድ ቤቶች የሚገኝ የከተማን ቤት የሚመለከት ክርክር በተባሉት ፍርድ ቤቶች ይታያል ።

፵ ፤ ክስ ስለማገድ ፤

፩/ ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን ጀምሮ በመደበኛ ፍርድ ቤት የሚገኝ የከተማን መሬት የሚመለከት ክርክር ተሠርዟል ።

፪/ ይህ አዋጅ በሚሰጠው ሥልጣን መሠረት የሚወሰደውን እርምጃ ሕጋዊነት ለመቃወም ማናቸውንም ክስ ፤ ወይም ይግባኝ ለመደበኛ ፍርድ ቤቶች ለማቅረብ አይቻልም ።

3/ The Ministry shall ensure that the rents collec[ted by] a co-operative society are utilized for providi[ng ser]vices to the urban dwellers in accordance with [com]prehensive urban development plans and di[rectives] issued by the Government.

4/ The Ministry shall be responsible for the [overall] administration of urban lands and urban [houses] belonging to the Government.

5/ The Ministry shall, by issuing urban developmen[t plans] and building economical houses, provide e[ssential] services to urban dwellers.

6/ The Ministry shall, in co-operation with the M[inistry] of Interior and co-operative societies of urba[n dwel]lers, provide landless urban dwellers with urb[an land] for building dwelling houses.

7/ The Ministry shall issue standards relating to houses and enforce the same.

8/ The Minister or the person or organization de[signated] by him shall fix the rents of houses not rented [on the] effective date of this Proclamation.

37. *Rights of Inquiry*

The person designated by the Ministry shall have t[he right] to inquire into and obtain contract documents an[d other] information from Government offices, private, com[mercial] and co-operative organizations and persons.

CHAPTER VII

GENERAL PROVISIONS

38. *Juridical Personality of Co-operative Societies*

Each co-operative society of urban dwellers establ[ished at] any level under this Proclamation shall have its ow[n juridi]cal personality.

39. *Jurisdiction of Ordinary Courts of Law*

Disputes under Article 17 (3) and disputes involvi[ng urban] houses pending in ordinary courts of law on the [effective] date hereof shall be heard in such courts.

40. *Prohibition of Court Action*

1/ All cases involving urban land pending in the [ordinary] courts of law on the effective date hereof ar[e hereby] annulled.

2/ No suit may be brought challenging the le[gality of] any action taken pursuant to the provision[s of this] Proclamation.

፵፩ ፤ ወንጀሎች ፤

ይህ አዋጅ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ቤት ወይም ንብረት ያቃጠለ ፤ ጉዳት ያደረሰ ፤ ያፈረሰ ፤ ያበላሸ ፤ ወይም ከጥቅም ውጪ እንዲሆን ያደረገ ወይም የሞከረ ፤ ፀጥታ ያደፈረሰ ወይም ለማደፍረስ የሞከረ ወይም በማንኛውም ሁኔታ አዋጁ በሥራ ላይ እንዳይውል ያሰናከለ ወይም ለማሰናከል የሞከረ ፤ እንዲሁም ማንኛውም ባለሥልጣን ወይም የመንግሥት ሠራተኛ በአዋጁ በተሰጠው ሥልጣን ወይም ኃላፊነት ያለአገባብ የተጠቀመ ወይም ለመጠቀም የሞከረ ማንኛውም ሰው በልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አዋጅ ቍጥር ፰/፲፱፻፷፯ ዓ. ም. ከነማሻሻያው በተደነገገው መሠረት ይቀጣል ።

፵፪ ፤ ከሌሎች ሕጎች ጋር ስላለው ቅራኔ ፤

ማንኛውም ሕግ ፤ ደንብ ፤ የተለመደ አሠራር ወይም ሥነ ሥርዓት የተጻፈም ቢሆን ሳይጻፍ በልማድ የሚሠራበት ሁሉ ይህን አዋጅ የሚቃረን ከሆነ ተፈጻሚነት አይኖረውም ።

፵፫ ፤ የዲፕሎማቲክ ይዞታዎች ፤

ይዞታው የዲፕሎማቲክ ፤ የቆንሲላ ፤ ወይም የኢንተርናሽናል ድርጅቶች የሆነ የከተማ ቦታ ወይም ንብረትነቱ የእነዚሁ የሆነ ቤት ሁኔታ ወደፊት ይወሰናል ።

፵፬ ፤ አዋጁ የማይጸናባቸው ቤቶች ፤

የሃይማኖት ድርጅቶች ንብረት በሆኑ የጸሎት ቤቶች ላይ ይህ አዋጅ ተፈጻሚነት አይኖረውም ።

፵፭ ፤ ደንብ የማውጣት ሥልጣን ፤

ሚኒስትሩ የአዋጁን አንቀጾች ዓላማ በሚገባ ለማስፈጸም ደንቦችን ለማውጣት ይችላል ።

፵፮ ፤ አዋጁ ስለሚጸናበት ቀን ፤

ይህ አዋጅ ከነሐሴ ፩ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፱ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ. ም.

ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ።

41. *Offences*

Any person who, as of the date of the promulgation of this Proclamation, burns, damages, destroys, tampers with or puts out of use any house or property, or disturbs the peace or obstructs the execution of this Proclamation or attempts to commit any of these offences and any Government official or public servant who misuses or attempts to misuse the authority vested in him under the provisions of this Proclamation shall be punished under the provisions of the Special Penal Code Proclamation No. 8/1974, as amended.

42. *Conflict with Other Laws*

No law, regulation, practice or procedure, whether written or customary, shall, in so far as it is inconsistent with the provisions of this Proclamation, have force and effect in respect of situations provided for by this Proclamation.

43. *Diplomatic Holdings*

The status of urban lands held and urban houses owned by diplomatic and consular representatives and international organizations shall be determined in the future.

44. *Houses to which this Proclamation is not Applicable*

This Proclamation shall not apply to urban houses owned by religious organizations which are used for conducting religious services.

45. *Power to Issue Regulations*

The Minister may issue regulations to give effect to the purposes and provisions of this Proclamation.

46. *Effective date*

This Proclamation shall enter into force as of 7th August, 1975.

Done at Addis Ababa, this 26th day of July, 1975.

THE PROVISIONAL MILITARY ADMINISTRATIVE COUNCIL

ሳሙኤል ግርማ
የሕግ አማካሪና ጠበቃ
Samuel Girma
Legal consultant and Attorney
+251911190299